# የምስራች!!!

2018-12-30

**ለተወደዳችሁ የኢየሩሳሌም ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን ምእመናን፣**

**የታዳጊ ወጣቶች አገልግሎት** በአማርኛ የእግዚአብሔርን ቃል መማርና አምልኮን ማካሄድ ለሚቸገሩና እዚህ ምድር ተወልደው ላደጉ ታዳጊ ወጣቶቻችን በቤተክርስቲያናችን ታቅፈውና ቤተኝነት ተስምቶአቸው ቤተክርስቲያንን ተረካቢ ሊሆኑ እንዴት እንደሚችሉ ሲያስብ ሲያወጣ ሲያወርድ ቆይቷል። ይህ አገልግሎት ከአንድ አመት በፊት ጀምሮ ስለዚህ ጉዳይ ሲጸልይና እንዴት ተግባራዊ እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚቻል ከቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችና ከወጣቶች ወላጆች ጋር ሲመካከር ቆይቷል። በመጨረሻም ሁለት እርምጃዎችን ለመውሰድ በዝግጅት ላይ ይገኛል።

> **1ኛ) ከ17 ዓመት በላይ እድሜ ያላቸው ወጣቶቻችን እሁድ እሁድ በሚኖረን የቤተክርስቲያን የአምልኮ ጊዜ ላይ በተለያዩ አገልግሎቶች እንዲሰማሩ።**
>
> **2ኛ) ከአርብ ጃንዋሪ አራት 2019 ጀምሮ ዘወትር አርብ አርብ ምሽት ከ18 ሰዓት እስከ 22 ሰዓት ድረስ የሚቆይና በስዊድንኛ አምልኮ የሚካሄድበት ጉባኤ እንድናዘጋጅና ይህም ጉባኤ ስዊድንኛ ተናጋሪ ለሆኑ ወጣቶችና ታዳጊ ወጥቶች የአገልግሎት እድል በመስጠት ላይ ያተኮረ እንዲሆን ወስነናል።**

ከላይ እንደገለጽነው ይሄንን የስዊድንኛ ጉባኤም እንዴት ተግባራዊ እንደምናደርገውም ከቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችና ከወላጆች ጋር በስፋት ተመካክረናል።

ስለዚህ ምናልባት ቅዳሜ 2018-12-15 በመካከላችን ያልተገኛችሁ ወላጆችም ሆናችሁ ምእመናን አርብ ጃንዋሪ አራት 2019 ጀምሮ የስዊድንኛ ጉባኤን በቤተክርስቲያናችን የምንጀምር መሆናችንን በታላቅ ደስታ እናበስርላችኋለን - **የምስራች**!! ወደፊት በመንገድ ላይ ለማንኛውም ዜጋ ሰዎች መስክረን ወደቤተክርስቲያን ስንጋብዛቸው መጥተው በገዛ ቋንቋቸው ስብከትና አምልኮ የሚሰሙበት፣ ልጆቻችንም በቀላሉ ያላንዳች የቋንቋ ገደብ የሚያገለግሉበትን ጉባኤ በአዲሱ አመት (2019) እንጀምራለን። አጥቢያ ቤተክርስቲያናችን ይሄንን ምድር ከመቼውም በላይ ለመድረስ የምትዘረጋበትና ወንጌልን በልጆቻችን ውስጥ ለዚህ ሕብረተሰብ የምናደርስበት ጊዜ ደርሷል!!! እግዚአብሔር ይመስገን።

በዚህ አጋጣሚ በትንሹ ስለሚጀመረው ስለዚህ አዲስ ጉባኤ እንድትጸልዩና እንድትማልዱ በጌታ ትህትና እየለመንን ሰዎችን ከገሃነም ፍርድ ለማዳን፣ ወደሞት የሚነዳውን የዚህን ምድር ወጣት ሁሉ ከሰይጣን መንጋጋ ለመታደግ፣ ብዙ ስዊድናውያን ወጣቶች መጥተው በመንፈስ ቅዱስ የሚሞሉበት ስፍራ እግዚአብሔር እንደቃሉ እንዲያደርጋት አጥብቃችሁ እንድትጸልዩ በድጋሚ እናሳስባለን።

እግዚብሔር ይባርካችሁ!
***የታዳጊ ወጣቶችና የስዊድንኛ ተናጋሪ ወጣቶች አገልግሎት***